# ቀንበር እናንሳለት

አገሬ ከስዊድን
20100528

በጎሳ ከፋፍሎን ፤ እኛ ስንናቆር
አይገዙ ተገዛን ፤ ተደልድለን በዘር ።

*ኧረ የሰዉ ያለህ ፤ ተቆርቋሪ ለአገር*
*ምን ጥቅም ተገኘ ፤ ከአለፍንበት ነገር ።*

እራስ ወዳድነት እኔ ፤ ያልኩት ብቻ
መማረር አበዛ ፤ እርስ በእርስ ጥላቻ ።
እኔ የሀይሉ ነኝ ፤ እኔ የብርቱካን
እኔ የግዛችው ፤ እኔ የመስፍን
መራራ በየነ ፤ ብሎም ልደቱን
ብርሀኑን ለቀቅ ፤ አትጥሩ ስዬን
የምን ሰላማዊ ፤ ያዘው ከፋኝን
ቀደምቶቹም አሉ ፤ ኢህአፓ ፤ መኢሶን
መባባሉ ቀርቶ ፤ መተቸት ማብዛት
መናቆሩ ቀርቶ ፤ በነገር መዉጋት
ዉጡ እንተባበር ፤ ለህዝብ ነጻነት ።

*ኧረ የሰዉ ያለህ ፤ ተቆርቋሪ ለአገር*
*ምን ጥቅም ተገኘ ፤ ከአለፍንበት ነገር ።*

መከራ ላይ ወድቆ ፤ ህዝብ ሲማጸን
ከኛ ይጠበቃል ፤ በሕብረት መሆን ።
ከአብራኩ ወጥተናል ፤ በደም ቁርኝት
እየከፋ መጥቷል ፤ የኑሮው ጥልመት ።
ታፍኖ ህዝባችን ፤ አድኑኝ እያለ
እርምጃችን ይሁን ፤ እየተስተዋለ ።

*ኧረ የሰዉ ያለህ  ፤ ተቆርቋሪ ለአገር*
*ምን ጥቅም ተገኘ ፤ ከአለፍንበት ነገር ።*

ዉነት ሀሳባችን ፤ ለሀገር ከሆነ
ዉነት ጭንቀታችን ፤ ለወገን ከሆነ
እርምጃችን ሁሉ ፤ ይሁን የሰከነ ።
ትብብር ይደረግ ፤ በህብረት መስራት
ዉጥኑ አይረሳ ፤ ይኑረን ብቃት ።

አጉል ግትርነት ፤ ወደሗላ ቀርቶ
ልዩነት አክብሮ ፤ በጋራ ተነስቶ
በጥምረት መስራት ነው ፤ የምን እንቶ ፈንቶ
መነቋቆር ይብቃ ፤ ውጥኑ ተረስቶ
በቃለ መሃላ ፤ በፅናት ተሞልቶ
አምባጓሮዉ ይቅር ፤ ወያኔን ጎልቶ
ህዝቡ ማየት ይሻል ፤ ወያኔ ተመቶ ።

EthioLion.Com

*ኧረ የሰዉ ያለህ ፤ ተቆርቋሪ ለአገር*
*ምን ጥቅም ተገኘ ፤ ከአለፍንበት ነገር ።*

ርሀቡ ጥማቱ ፤ ጨለማው ሳያንስ
በጎሳ ከፋፍሎ ፤ ህዝብ ሲጫርስ
ወደብ አልባ ስትሆን ፤ ኢትዮጵያ ስታንስ
ዝርፊያውን ቅሚያውን ፤ ችሎ ቢታገስ
እየባሰ መጣ ፤ በጥይት ማመስ
ንቆ ደነፋበት ፤ አለው አትተንፍስ
ቁጭ ብለን አንይ ፤ ህዝብ ሲታመስ ።

*ኧረ የሰዉ ያለህ ፤ ተቆርቋሪ ለአገር*
*ምን ጥቅም ተገኘ ፤ ከአለፍንበት ነገር።*

ተከፍለን ተከፍለን ፤ ስንልፈሰፈስ
ያበጠ ወያኔ ፤ አገር ሳይጨርስ
በተባበረ ክንድ ፤ በህብረት ይደምሰስ ።
ሞትን የሚያስመርጥ ፤ ስቃይ እያለበት
በህብረት እንቁም ፤ አንቀልደበት
ለጋራ አላማችን ፤ ለወገን ነፃነት።
ከህዝቡ ጫንቃ ላይ ፤ ቀንበር እናንሳለት።

EthioLion.com